# እኔ ለእኔነቴ

ሩቅም ቦታ ኣልሄድኩ፣ ያለሁ ከሃገሬ
ተቀምጬ ስኖር ከቤት፣ ከሰፈሬ
ያየኝ ሰው ከሳተኝ፣ ከመሰልኩት ኣውሬ
እሪ ልበል ይሆን፣ ወይ ላልቅስ ኣምርሬ!

መልኬን፣ ፊቴን ኣይቶ ያውቀኝ እንደሆን
"ማነኝ እኔ?" ብዬ ብጠይቅ ሰዉን
ተመልክቶ ሲያልፈኝ ከመንገድ ኣሁን
ኣንድም ሰው ኣጣሁኝ፣ ከንቱ መባከን!

ሌላው ሰው ላያውቀኝ በሰብኣዊነቴ
ወረቀት ሆነና የኔ ማንነቴ
ኣፈር ለለበሰው መላው ሰውነቴ
ኣልገባህ ብሎኛል እኔ ለእኔነቴ።

እንደዚህ እየኖርኩ በዓለም ከተማ
እኔ ማንነቴን ካላወቅኹትማ
ተበላሸ፣ በቃ፣ ምን-ምኑም ኣይለማ
ጠላቴ እኔ እንጂ ሌላው ኣይደለማ!

ብፈትሸው ኪሴን፣ ቋቴን፣ ከረጢቴን
ከመታወቂያው ላይ ላየው ማንነቴን
መዓርግ ካለኝም እንዳውቀው ሹመቴን
ማነው የሚያስረዳኝ ይህ ሓላፊነቴን?

እኔ ከውስጥ ሆኘ በሓሳብ ስዋኝ
ሰዉም ከውጭ ሆኖ የጎሪጥ ሲያየኝ
"ዕብድ ነው፣ ጤነኛ?" እያለ ሲያልፈኝ
ማንነቴን ማወቅ ጭራሽ ተሳነኝ።

ይቅርስ ለሌላ ለኔው፣ ለእኔነቴ
በውል ካልታወቀኝ ለኔ ማንነቴ
ከምኑ ላይ ይሆን ተጠያቂነቴ
ኣውርጃለሁ ቀርቷል ያ ሓላፊነቴ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።

Back to Meskot

---

*The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by Meskot. You may contact G.E. Gorfu for comments at gegorfu@yahoo.com.*